## “ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱንም ሰጠ።” (ማር፤ምዕ፤15፥37-38)

## ሰሙነ-ሕማማት

ለፋሲካ በዓል ሁለት ቀን ሲቀረው
የካህናት አለቆች ተንኮል ሠሩ መክረው
ጌታችንን ለመያዝ ተቆጥተው ዝተው።
በምክራቸው መሀል ትዝ ሲላቸው
ህዝቡ እንደሚነሳ ተቃውሟቸው
በበዓል እንዳይሆን ፀና ምክራቸው
በለምፃሙ ስምዖን ቤት ማዕድ ተዘጋጅቶ
ጌታችን ተገኘ ሁሉንም አሳክቶ
ሐዋርያትንም ሰብስቦና ጠርቶ።
በዚህ ቤት ኢየሱስ ተቀምጦ ሳለ
የአንዲት ሴት ስጦታን በዕውነት ተቀበለ።
ያቺም ሴት በዓለም ላይ ዘማዊት ነበረች
ኢየሱስን ክዳ ኰብልላ የኖረች
በጊዚያዊ ጥቅም ለስጋዋ ያደረች።
የማታ የማታ ተፀፅታ አዝና
በልቧ አቀረበች ለአምላክ ልመና
ወደሱ ጋ ሄዳ ለመመለስ ድና።
አስባም አልቀረች ሄደች ገሠገሠች
እጅግ የከበረ ሽቶም ይዛ መጣች
ጌታዋን ለማየት ነፍሷ እየናፈቀች።
ብልቃጡንም ሰብራ ራሱ ላይ አፈሰሰች
በቀድሞው ስራዋ እየተፀፀተች
በዓለም ውስጥ መኖር መርገም ነው እያለች።
መልካም ስራዋንም ጌታችን አክብሮ
እንዲያስተናግዷት ለሐዋርያት ነግሮ
ነፃነት ማግኘቷን ደስታዋን አብስሮ
በዕውነት ባረካት ሁሉን አስተምሮ።
ይህን ድንቅ ስራ አማኑኤል አውቆ
ስለሞቱ ነገር አሰማ ጠንቅቆ።
የዚች ሴት ስራ በዓለም እንዲወራ
የሰው ዘር ባለበት በየትኛውም ስፍራ
በበጐ ተግባሯ እንድትኖር ተከብራ
ቃል ገብቶ ሰደዳት በሷም ላይ አበራ።
የጌታ ሐዋርያ የአስቆሮቱ ይሁዳ
ተነሳሳ ልቡ ጌታውን ሊከዳ
አሳልፎ ሊሰጠው አድርጎ ባለ ዕዳ
ሁሉንም ጨርሶ ለመሄድ ተሰናዳ።
የካህናት አለቆች ይህንን ሰምተው
ባጋጣሚው ነገር ደስታን አግኝተው
ወሰኑ ለመስጠት ገንዘብ አውጥተው
ለዛ ላልታደለ ለሚያሳዝን ሰው።
ይሁዳ አታላዩ ምቹ ጊዜ አገኘ
ጌታውን ለመሸጥ ልቡ እየተመኘ
ለስጋው ብቻ አድሮ ለነፍሱም አልዳኘ
ከጠላት ዲያብሎስ ጋር ፍፁምተቆራኘ
የጌታ ሐዋርያት ተቀምጠው ሳሉ
ማዕድ ቀርቦ እራት እየበሉ
በኢየሱስ አንደበት ይህንን ተባሉ
ከእናንተ መሀል እዚህ ካላችሁት
እኔን አሳልፎ የሚሰጥ አለበት
ለዛ ሰው ግን ዛሬ ወዮታ ሆነበት
ይሻለው ነበረ ባይወለድ በዕውነት።
ጌታ ይህንን ሲል ሁሉም ደንግጠው
እርስ በራሳቸው ተያዩ ፈርተው
እኔ እሆን እኔ እሆን አሉ ጠይቀው
መልሱን ከጌታቸው ለማግኘት ሽተው
ከኔ ጋር ወደ ወጭቱ እጁን ያጠለቀ
ያ ነው ወንጀለኛ ጌታውን የናቀ
ኃጢአትን ለመስራት የተጠናቀቀ።
ኢየሱስም ባርኮ ሰጣቸው እንጀራ
ፅዋውን አንስቶ አደለ በተራ
የአባቱንም ስም አመስግኖ ጠራ።
ሐዋርያት ሁሉ ከቀረበው ጠጡ
መዝሙርም ዘምረው
ወደ ደብረ ዘይት ወጡ።
እንደገና አሁንም በጣም ተጨነቁ
ጌታ የሚለውን ምንም አላወቁ
ሌሊት ተሰናክለው
ለምን እንደሚወድቁ።
ጴጥሮስ በከፍታ ድምፁን አሰምቶ
አልሰናከልም መቼም ቢሆን ከቶ
እያለ ፎከረ በወኔ ተሞልቶ።
ኢየሱስ ግን ወዲያው ጴጥሮስን እያየ
የሚክድበትን ሰዓት ሁሉ ለየ።
ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ
ጌታችን አመራ ከሐዋርያት ጋራ
ፀሎት ለመፀለይ ለመጣው መከራ።
ቢቻል ይቺ ፅዋ እኔ ጋ አትድረስ
ነፍሴ እጅግ አዘነች እስከሞት ድረስ
ብሎ ተናገረ በፀሎት መንፈስ
ዳግማዊው ዓዳም ኢየሱስ ክርስቶስ።
የአባቱን ፈቃድ ሊፈፅም የመጣው
የሰዎችን በደል በራሱ ላይ ያኖረው
ፈቃድህ ይሁን ብሎ ለአባቱ ነገረው

የፊቱን መከራ ጠንክሮ ሊችለው።
የሰው ልጆች ኃጢአት የሚደመሰሰው
የዲያብሎስ ሽንገላ ጭራሽ የሚጠፋው
ከነሰራዊቱ ሲያል የሚጣለው
ፍቅርና ሰላም በዓለም የሚሰፍነው
የተስፋችን ብርሃን ዕውን የሚሆነው
ጥልና ክርክር ሥሩ የሚነቀለው
በእርሱ በራሱ መሆኑን አወቀው
በሥጋ ለመሞት ጉዞውን ጀመረው
መጨነቅ መጠበብ ትካዜውን ተወው።
ጸሎቱን አድርሶ ሲመለስ ጌታችን
ተኝቶ አገኛቸው ደቀ-መዛሙርቱን
መትጋት አቅቷቸው አንዲት ሰዓት እንኳን።
ፈተና እንዳይገቡ ጸልዩ አላቸው
መንፈስ መበርታቱን ገልፆ ነገራቸው
እነሱ ግን እንቅልፍ በጣም ከበዳቸው።
የዓለምን በደል ለመሻር የመጣው
ሞትን ድል ለመንሳት ዝግጁ የሆነው
ከኃጢአት ባርነት ሰው የሚያላቅቀው
ለደካሞች ብርታት ሆኖ የሚኖረው
ለሰው ልጆች ሁሉ ዕውቀትን ያደለው
በጥበብ በሞገስ በዚህ ዓለም ያደገው
በክፉዎች ሰዎች እጅ አልፎ ሊሰጥ ነው።
ጌታ ከሐዋርያት ጋር ለመሄድ ሲነሳ
ይሁዳ ደረሰ ስሙን እያወሳ
ለካህናት አለቆች ሊሰጠው ሳይሳሳ።
ከይሁዳ ጋርም ብዙዎች ነበሩ
ፃፎችና ካህናትም መጡ እየፎከሩ
ሰይፍና ጎመዱን ፊቱ እያማተሩ።
ይሁዳ ጨካኙ ልቡ ሸፍቶበት
ፍቅረ-ነዋይነት ዓይኑን አሳውሮት
ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ረግጦ ገዝቶት
ያን ሁሉ ውለታ ጨርሶ ዘንግቶት
ጌታውን አሳልፎ ሰጠው ይኸው ለሞት
የሚወደው መስሎ እንደ ወዳጅ ስሞት።
እጃቸውን ጭነው ጌታችንን ያዙት
ቀድሞ የተፃፈውን ትንቢቱን ፈፀሙት
በምኩራብ ሲያስተምር ለምን እንደተዉት።
ፃፎችና ካህናት አጅበው ሲወስዱት
ደቀ-መዛሙርቱ ፈርተው ጥለው ሸሹት።
ጴጥሮስ ግን ከሩቁ እየተከተለው
እስከ ሊቀ-ካህኑ ግቢ ድረስ ሸኘው።
ፃፎችና ካህናት ምክንያት ፈልገው
ኢየሱስን ቀጥቶ የሚያስገድለው
አጡ ምስክር ሰው ቃል የሚሆናቸው።
ስለዚህ አንድ በአንድ ሁሉ እየተነሳ
በሐሰት ምስክር ጀመሩ ከሰሳ
እንዲያገኘው ፍዳ መከራና አበሳ።
በስንት ጥበበኞች ታልሞ የተሰራ
የኛን ቤተ-መቅደስ ልክ እንደማይረባ
አፍርሶ በሶስት ቀን አንፆ ሊሠራ
ሲናገር ሰምተናል ማንንም ሳይፈራ
እያሉ አሳጡት ከቀኝ ከግራ
በፍርድ አደባባይ አቁመው እንደተራ።
ሁሉም የየራሱን ክስ ቢናገርም
ጌታ ግን ዝም አለ ምንም አልመለሰም
ዝምታው ሲበዛ እጅግ በመደነቅ
የኢየሱስን ማንነት ፈልጎ ለማወቅ
የብሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን?
እያለ ጠየቀው የአይሁድ ሊቀ-ካህን።
በዚህን ጊዜ ኢየሱስ ዘና በማለት
አዎን ነኝ ሲል ቃሉን ደገመለት
የብሩክ ልጅ መሆኑን መሰከረለት
ዳግም እንደሚመጣም አበሰረለት
በሰማይ ደመና ሰዎች እያዩት።
ሊቀ-ካህናቱም ይህንን ሲሰማ
ምስክር ለማግኘት ምንም አላቅማማ
በቅፅበት ቀደደው ያደረገውን ሸማ
የኢየሱስንም ቃል ስድብ ብሎ አሰማ።
ኢየሱስን ከስሰው ለፍርድ ያቆሙት
ሐሰትን ተናግረው ዕውነት ነው ያሉት
በአንድ ድምፅ ሆነው ሞት ፈረዱበት።
ጎባጦችን ባቀና
ዕውራንን ዳብሶ ባበራ
ለምፃሞችን ባነፃ
የሞተውን ሬሳ ባስነሳ
አጋንንትን ባስወጣ
አመፀኞችን ይቅር ባለ
እንጀራን በዓሣ ባጠገበ
ውኃውን ወደ ወይን በለወጠ
የበጎች እረኛ ምን አደረገ
ምራቅስ መትፋቱ ለምን አስፈለገ
ፊቱ ተሸፍኖስ ለምን ተጎሸመ
በጥፊስ ተመትቶ ለምን ተነተተ
ሰውነቱ እሰኪቆስል ለምን ተገረፈ
ከሰራ አካላቱስ ለምን ደም ፈሰሰ
መጕናፀፊያውን ለምን ተገፈፈ
ለእኛ እኮ ሲባል ነው እኛኑ የወደደ
እራሱን አሳልፎ እራሱን የሰጠ።
የሊቀ-ካህኑ ገረድ የሆነችው
ጴጥሮስ እሳት ሲሞቅ ከሩቅ ስላየችው
ወደሱ ተጠግታ አጥበቃ ያዘችው

ከኢየሱስ ጋር ነበርክ ብላ አፋጠጠችው።
በባህር ላይ በእግሩ መሄዱን ረሳና
የቃናውን ተአምር ተራ አደረገና
የታቦርን ምስጢር ከቶ ዘነጋና
ሙሴና ኤልያስን እንዳላየ ሆነና
ግርማ መለኮቱን እንደው ቸል አለና
ማሰሪያና መፍቻ ቁልፉን ጣለውና
ውለታ ቢስ ሆነ ዓለቱ ቀረና
አላውቀውም አላት ጌታውን ከዳና
ታላቁ ሐዋርያ ተደናገጠና።
ተናግሮ ሲጨርስ ወዲያው ከመቅፅበት
ማስተዋል ጀመረ የዶሮውን ጩኸት
ጌታችን ያለውን አሰቀድሞ በፊት
ጴጥሮስ ተፀፀተ ባደረገው ስህተት
እንባውን አፍስሶ ራሱን ወቀሰበት።
በሸንጎ ተማክረው ጠዋት በማለዳ
ኢየሱስን ወሰዱት አድርገው ባለ ዕዳ
በጲላጦስ ታስሮ እንዲያገኘው ፍዳ
አገረ-ገዢውም ጥያቄ አቀረበ
በዕውነት የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን?እያለ
ኢየሱስም መልሶ እነሆ አንተ አልክ አለ።
የአይሁድ ካህናት ግብራቸው የከፋ
እኩይ መንፈሳቸው በጣሙን የበዛ
ጌታ እንዲገደል ነው ያደረጉት ሴራ
በርባን ነፃ ሆኖ ከእስር እንዲፈታ
ኢየሱስ ተሰቅሎ እንዲያገኙ እርካታ
ጲላጦስም አዝኖ የሚያደርገው ቢያጣ
ኢየሱስን ገርፎ በርባንን አሰወጣ
መገረፉ ብቻ በቂ ስላልሆነ
ሰቅለው እንዲወስዱት ለመስጠት ወሰነ።
የአይሁድ ወታደሮች እዛው የነበሩት
ፕራይቶሪያን ግቢ ኢየሱስን ወሰዱት
ጭፍራውን በአንድ ላይ ጠርተው ሰበሰቡት
ቀይ ልብስም መርጠው ጌታን አለበሱት
የሾህ አክሊልንም ጎንጉነው ደፉበት
ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ አሾፉበት።
በሰው ችግር ደርሶ ሁሉን የሚረዳ
ዛሬ እንደጠቦት በግ ዝም ብሎ ተነዳ
እኛኑ ለማዳን ከነበረን ፍዳ።
ምን ዓይነት ትእግስት ነው የማያልቅበት
ከቶ ዝም ያላቸው ሞት ሲፈርዱበት።
የራስ ቅል ስፍራ ጐልጐታ ሲደርስ
በድፍረት አመጡ ወይን ጠጅ እንዲቀምስ
ከርቤ ያለበትን ሐሞትን የሚያፈስ
ኢየሱስ ግን ተወው ምንም ነገር ሳይቀምስ።
አይሁድ አመፀኞች ያሰቡት ተሳካ
መትፋት መጎተቱ በመስቀል ተተካ።
ኢየሱስን ሰቅለው ዕጣ ተጣጣሉ
ልብሱን ገነጣጥለው ሁሉም ተካፈሉ።
በቀኝና በግራ ወንበዴዎች አድርገው
በመሐል ሰቀሉት በክፋት ተመልተው
እግርና እጆቹን በምስማር ቸንክረው።
ነቢዩ ኢሳይያስ አምላክ ያሳሰበው
በትንቢት ተናግሮ አስቀድሞ የፃፈው
ይኸው በጐልጐታ ሰቀሉት ተማክረው
እንደ አመፀኛ ወንጀለኛ ቆጥረው።
ምን ዓይነት ፍቅር ነው
ምን ዓይነት ምህረት
ፈያታዊ ዘየማን ከቶ የዳነበት
እንዴት ተከፈተች ገነት ለቀማኛ
ይቅር ብሎት እንጂ የበጎች እረኛ።
ሲዘርፍ ሲቀማ ሲገድል አድብቶ
ኑሮውን በሰው ደም ሠርቶና መስርቶ
በአንዲት ቃል ብቻ ድምፁን አሰምቶ
ማረኝ ሲል ለመነ ታምሩን ሁሉ አይቶ
ይቅር እንደሚለው በልቡ ተረድቶ።
ፀሐይ ስትታዘዝ ብርሃን አልሰጥ ብላ
ምድር ስትናወጥ ስታጣበት መላ
ጨረቃ ደም ስትመስል ጌታዋን ከልላ
ምን ዓይነት ዕድል ነው
ሌባ ይህን ማወቁ
ጌታ ሆይ አስበኝ እያለ ማድነቁ።
አብርሃም እያለ ለትውልድ የተጠራ
ሙሴስ እያለ እስራኤልን የመራ
ነቢያት እያሉ ስሙን የዘከሩ
እነ ዳዊት እያሉ ለክብሩ የዘመሩ
ቀድሞ የገባበት ምንድነው ምስጢሩ
ገነት ተከፍታለት ወለል ያለው በሩ
ከአእምሮ በላይ ነው ይህን መመርመሩ
በመስቀል እያለ እናቱን መች ረሳ
ዮሐንስ ፍቁረ-እግዚእን ሰሙን እያነሳ
የልጅ የእናትነት ሰጣቸው መዓዛ።
ስድስት ሰዓት አልፎ
ዘጠኝ ሰዓት ሲደርስ
ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ
ብሎ ጮኸ ኢየሱስ።
በዚያ የቆሙት ግን ትዕቢት የያዛቸው
ሁሉም ኤልያስን የጠራ መስሏቸው
ኤልያስ ያድነው ሆነ ውሳኔያቸው።
ከአይሁድ መካከል በፍጥነት ሮጦ
ሰጠው ለጌታችን ሆምጣጤ በጥብጦ
ይፈር ተስፋ ይቁረጥ

ዲያብሎስ አመፀኛው
ይንቀጥቀጥ ይርበድበድ
ይጥፋው መግቢያ መውጫው
ኢየሱስ ጌታ ነው የዓለም መዳኛው
ነፍሱን በፈቃዱ ሰጥቶ ይሁን ያለው።
ጊዜው ምሽት ነበር የሰንበት ዋዜማ
የአርማትያስ ዮሴፍ መጣ ሳያቅማማ
የኢየሱስን ሥጋ ለመውሰድ ሊስማማ
አውርዶም በበፍታ ጥሩ አድርጎ ከፈነው
በዓለት ከተሠራ መቃብር አኖረው።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ
ለንደን
መጋቢት 2002